ከነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጋር ሰገድኩኝ። ወደ ቀኛቸው "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱህ" በማለት ያሰላምቱ ነበር። ወደ ግራቸው ዞረው ደሞ "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ" ይሉ ነበር።

ከዋኢል ቢን ሑጅር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ከነቢዩ (ሶለላሁ
ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጋር ሰገድኩኝ። ወደ ቀኛቸው "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱህ" በማለት ያሰላምቱ ነበር። ወደ ግራቸው ዞረው ደሞ "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ" ይሉ ነበር።»
[ሐሰን ነው።] [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከሶላታቸው ማጠናቀቅ የፈለጉ ጊዜ ወደ ቀኝና ወደግራቸው ያሰላምቱ ነበር። ይህም "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላሂ ወበረካቱህ" እያሉ በፊታቸው ወደ ቀኝ አቅጣጫ ይዞራሉ። "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱላህ" እያሉ ደሞ ወደ ግራ አቅጣጫ ፊታቸውን በማዞር ወደግራ ያሰላምቱ ነበር።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/10945